# ጦር እንዳዋጊው፤ ልጅ እንዳሳዳጊው አንድም ገዳይ አንድም ሠናይ

አብርሃም በየነ

የማንኛውም ህፃን ልጅ የመጀመሪያ መምህሩ ወላጆቹ ናቸው። ለአንድ ህፃን እንደ ሰው ለመናገር፤ እንደ ሰውም በሁለት እግሮቹ ለመራመድና፤ ብሎም እንደ ሰው ለማሰብ የሚያስችሉት ትምህርት ቤቱና መምህራኑ ወላጆቹ ናቸው። የሰውነት ባህሪውን የሚወርሰው አበክሮ ከራሱ ወላጆች ይሆንና በዚሁ ላይ አካባቢው የሚያሳድርበት ተፅዕኖ ተጨምሮበት የህፃኑ ባህሪይ ይቀረጻል። ስለሆነም የሰው ልጅ ከዝንጀሮ ጋር ካደገ የዝንጀሮ፤ ከተኩላም ጋር ካደገ የተኩላ ባህሪይ ይዞ ያድጋል።

በጥንታዊት ህንድ በዱር (በጫካ) የተገኙ ሁለት ህፃናት ነበሩ። ህጻናቱን ያገኟቸው አዳኞች ነበሩ። በህጻናቱ የተኩላ ባህሪይ የተደነቁት አዳኞች ህፃናቱን ወደ ሰፈር ወሰዷቸው። የሚራመዱት እንደ ሰው በሁለት እግሮቻቸው ሳይሆን እንደ ተኩላ በአራት "እግሮቻቸው" ነበር። ሲናገሩም የሚያስደምጡት ድምጽና አመጋገባቸውን ጨምሮ የተኩላ ባህሪይ ነበረው። አድኞቹ እነዚያን ህጻናት እንደ ራሳቸው ልጆች ሊያሳድጓቸው ስለወሰኑ የሰው ባህሪይ ይይዙ ዘንድ ብዙ ጣሩ። ዳሩ አሳዳጊዎቹ የተኩላ ባህሪይ የተዋረሳቸውን ህጻናት ለመለወጥ ያደረጉት ሙከራና ህጻናቱም በፍጥነት ያሳዩት የባህሪይ ለውጥ ወደ ሙሉ የሰው ልጅ ባህሪይ ለመቀየር እድሉን ሳያገኝ ህጻናቱ ሞቱ። የሰው ልጅ ባህሪይ በስልጠና ከሠናይነት ወደ ፋሽሽትነት በቀላሉ የሚለወጥ መሆኑን ሌላው ገላጭ ኃይል ደግሞ የቶድ ስትራስ መፅሃፍ "ዘ ዌይቭ" ወደር አይገኝለትም።

በጊዜ ኅዳና ብዙ ዘመን ወደ ኋላ ተጉዘን ህንድ ውስጥ በተገኙት ህፃናት ለማየት የሞከርነውን የባህሪይ አወራረስ በደርጉ የ17 ዓመት ፋሽሽታዊ አገዛዝ በወጣቱ ሲንፀባረቅ በዚሁ በሰሜን አሜሪካ አብረውን ከሚኖሩ ከሁለት የኢሕአፓ አባላት ልጆች እናገኘዋለን። ልዩነቱ የፊተኞቹ የወረሱት ባህሪይ የተኩላ ሲሆን የኋለኞቹ ግን ደርጋዊ አረመኔ መሆኑ ነው። እነዚህ ሁለት ወጣቶች የተወለዱት ከኢሕአፓ ቤተሰብ ሆኖ ግን ያደጉት የደርጉን ፋሽሽታዊ ባህሪይ ተዋርሰው ነበር።

ከሁለቱ ወጣቶች አንደኛዋ ሳምራዊት ተስፋ ትባላለች። ሳምራዊት ወደ አሜሪካ ከመምጣቷ በፊት መንግሥቱን የምታውቀው "በቆራጥ መሪነቱ" እንጂ በፋሽሽትነቱ አልነበረም። ይህች ወጣት አይደለም የግራዚያኒ መንግሥቱን የራሷን አባት ማንነት እንኳ የማወቅ ዕድል ተነፍጓት ነበር ያደገችው። ሳምራዊት የህቡዕ ልጅ ሆና ነበር ያደገችው። ይህች የወላጆቿን ማንነት ሳታውቅ በህቡዕ ያደገች ወጣት አርበኛዋ ወደር አልቦው አባቷ የኢሕአፓው መሪ ተስፋዬ ደበሳይ ሳይሆን የአባቷ ገዳይ ግራዚያኒ መንግሥቱ ነበር።

የደርጉ ዘመን ወጣት ባልተቋረጠ ፋሽሽታዊ ፕሮፖጋንዳ ስብዕናው ተገፍፎ የደርግን የግፍ ግድያ በወንጀለኛነቱ ሳይሆን የሚያውቀው በአብዮተኛነቱ ነበር። ያ የደርግ ደጋፊ ወጣት በደርግ አፋኞች እየተገደሉ በወላጆቻቸው በራፍና መንገድ ላይ ይጣሉ ለነበሩት ወጣት ኢህአፓዎች የሚደማ ልብ እንዳይኖረው ተደርጎ ነበር ያደገው።

የሳምራዊት ልብም አሜሪካ ገብቶ እስኪ ቀየር ድረስ ኢ.ሕአፓን ያየው የነበረው እንደ ዘመኗ ወጣት በደርግ ጠላትነቱ እንጂ በሕዝብ ጠበቃነቱ አልነበረም።

የሳምራዊት ወላጆች ለትግሉ ህይዎታቸውን ለመስጠት ቆርጠው የተነሱ አብዮታዊያን ስለነበሩ ህጻኗን ለማሳደግ እድሜ እንደማይኖራችው ያውቁት ነበርና ለደህንነቷ ሲሉ ሳምራዊትን ማነነቷ ሳይታወቅ ከአጎቷ ጋር እንድታድግ አደረጉ። እርሷም አሜሪካ እስከ መጣችበት ጊዜ ድረስ አቶ ተስፋ አባቷ እንጅ አጎቷ መሆናቸውን ሳታውቅ ኖረች።

ደንቆሮ የሰማ ዕለት ያብዳል እንዲሉ ሳምራዊት እውነታው እንደ ተገለፀላት ያነሳችው ጥያቄ ቢኖር ኢ.ሕአፓ እንዴት ከመኢሶን ጋር ህብረት ይፈጥራል? የሚል ነበር።

ሌላው አባቱ ኢ.ሕአፓ የነበረውና አቶ ክፍሉ ታደሰ "ያ ትውልድ" የተሰኘውን መፅሃፋቸውን ለመፃፍ ምክኒያት ሆነኝ የሚሉት ወጣት ገጠመኝም እንደ ሳምራዊቱ ገጠመኝ አስደማሚ ነው።

ከእለታት በአንደኛዋ ቀን አቶ ክፍሉ ታደሰ ወደ ድሮ ጓዳቸው ቤት ጎራ ይላሉ። ሁለቱ ጓዶች እንደ ወትሯቸው የድሮ የትግል ትውስታ ቀስቅሰው ያለፉብትን የትግል ሰቆቃ አንስተው ሲጥሉና በሰቀቀኑም ህሊናቸውን ሲያስቆዝሙ፣ በድሮ ጓዶቻቸው ሞትና አሟሟት፣ በደርጉም የጭካኔና የግፍ አገዳደል የፊታቸው ገፅታ ሲቀያየርና ግምባራቸው ሲገመድ- ሲፈታ የጓዱ ልጅ አጠገባቸው ተቀምጦ ወጋቸውን በጥሞና ያዳምጥ ኖሯል።

ወጣቱ ልጅ እስከዚያች ቅፅበት ድረስ የአባቱን ኢ.ሕአፓነት አያውቅ ስለነበር በሚሰማው ወግ ቆሽቱ አሯል። እርሱም እንደ ሳምራዊት "መንጌ" ይለው ለነበረው ግራዚያኒ መንግስቱ ይሰጠው ለነበረው ክብር ጥብቅና ቆሞ ቆሽቱ ያርና ይጨስ ነበር። አባቱ ከድሮ ጓዱ ጋር የጀመረውን ወግ እስኪ ጨርስ አቅል ጠቦት የነበረው ወጣት ክፍሉና አባቱ ወጋቸውን ጨርሰው ሲሰነባበቱ ወደ አባቱ ጠጋ ብሎ "አንተም ኢ.ሕአፓ ነበርክ እንዴ? አፈርኩብህ" እስከ ማለት ደርሷል።

ደርጉና ባንዳ ምሁራን ይገዙት የነበረውን ህዝብ ስብዕናውን ፍቀው የአውሬነት ባህሪይ ለማላበስ 17 ዓመት ወስዶባቸዋል። ይህ ስብዕናውን የተገፈፈ ህዝብ በደርግ በግፍ ለተገደሉት ወጣቶች ስብዕና መነፈግ የሚደማ ልብ እንዳይኖረው አስቀድሞ ነበር የራሱን ስብዕና የተገፈፈው። የደርጉ ወጣት እየተጎነጨ ያደገው የሰማዕታቱን ጥቁር ደም ስለነበር ያ የግፍ ደም ዛሬም ድረስ እንቅርት ሆኖት አዙሮ የሚያሳይ አንገት አስጥቶታል።

ኢ.ሕአፓ በቀይ ሽብር ተመትቶ መዋቅሩ ሲበጣጠስ ከፊሉ ታፈኖ በማጎሪያ ቤት፣ ስየል ሲፈፀምበት፣ ከፊሉም እግሩ ወደ መራው አቅጣጫ ለስደት ተዳርጓል። ደርግም ይህን አጋጣሚ ተጠቅሞ በስሩ የነበረውን ህዝብ በአምሳሉ ለመቅርጽ ሰፊ ሊያገኝ ችሏል። ይህ በደርግ አምሳል የተቀረጸው ህብረተሰብ ነው ዛሬ አንድም ለወላጁ ግፍ አግቦነት አንድም ለራሱ የዕንግዴህ ልጅነት ጥብቅና ቆሞ የሚጮኸው።

በሰሞኑ የፖለቲካ ግርግር የፕሬስ ነፃነቱ ተገፈፈ በሚል የጀማ ፍርድ (mob justice) የደርጉን ቅጥ ያጣ ግድያ አግባብነት የነበረው ጭፍጨፋ ለማስመሰል እነ ፕሮፌሰር ዓለማየሁ ከግራዚያኒ መንግሥቱ ጎን ተኮልኩለዋል። ፕ/ር ዓለማየሁና ሁለቱ ኤሊያሶች የደርጉ የሥርዓት ልጆች ናቸው። እነዚህ የሥርዓቱ ልጆች አባቱ ገዳይ ልጁም በዳይ እንዲሉ ነው የሰሞኑ የፖለቲካ ሰልፋቸው።

እነዚህ የዕፉኝት ልጆች የደርጉን ግፍና በደል ለመከላከል ዘብ የቆሙት ያለ ምክኒያት አይደለም። ትናንት ሥርዓቱ አቀዳጅቷቸው በነበረው ስልጣን የቤተሰባቸው የዕለት ጉርስና የጫንቃ ጨርቅ አቅርቦቱ እንዳይጓደል የኢሕአፓ ተቃውሞ በቀይ ሽብር መወገድ በነርሱ እይታ አግባብነት ነበረው። ያንዱ ሞት ለሌላው ድሎቱ ነው እንዲሉ ለነዚህ የዕፉኝት ልጆች የተሟል ህይዎት ዋስትና ሲባል የሰማዕታቱ ወላጆች ገመድ ታጥቀው እንዲኖሩ ተፈርዶባቸዋል።

የመንግሥቱ መጽሐፍ ለንባብ መብቃቱ ለነዚህ የዕፉኝት ልጆች ሁለት ዓይነት ጠቀሜታ ሲለግስ ይታያቸዋል። አንደኛው መጽሐፉ የደርግን ወንጀል በማድበስበስ ከታሪክም ሆነ ከህግ ወንጀለኛውን ነፃ ያደርገዋል የሚል እንደምታ ሲኖረው በሌላው መልኩ ደግሞ የወላጆቻቸው ገመና አለመጋለጡ የሥርዓቱን ልጆች “ንጹህ ሰውነት” ስለሚያረጋግጥ በተቃዋሚነት ተሰልፈው ወደፊት ስልጣን ለመያዝ ለሚያደርጉት ጉዞ እንቅፋት አይሆንባቸውም። ስለሆነም ዶሮ ለብልሃቷ ተንጋላ ትጠጣለች እንዲሉ እነ ፕ/ር ዓለማየሁ ለግራዚያኒ መንግሥቱ የፕሬስ ነፃነት ጥብቅና ቆመዋል።

እዚህ ላይ አንባቢ ልብ እንዲለው የሚያስፈልግ አንድ ነገር አለ። ይኸውም ባለፉት ሃያ ዓመታት ውስጥ ህብረትና ቅንጅት ለመፍጠር በኢሕአፓ የተሞከረው ሙከራ ሁሉ የዕንቧይ ካብ እየሆነ ሲናድ የኖረው በነዚህ የዕፉኝት ልጆች ደባና ሴራ እንደነበር ነው። የደርግ የዕንግዴህ ልጆች ከኢሕአፓ ጋር ህብረትና ቅንጀት ሲፈጥሩ የሚፈጥሩት ህብረቱ እነርሱን ወደ ስልጣን የሚያስወጣ እስከ ሆነ ድረስ ነው ደጋፍ የሚቸሩት። የህብረቱ ግብዓት ይህ ሳይሆን ቀርቶ ግን በምትኩ ኢሕአፓን ለስልጣን የሚያበቃ ሲመስላቸው ሲንዱት ኖረዋል። ለወደፊቱም ይንዱታል።

የነርሱን “ተቃዋሚነት” ትናንት አጣጥመው ሳይበሉበት የፈረሰው የደርግ የግፍ ሥርዓት የሚመለስበትን መንገድ መሻት እንጂ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከወያኔ ዘረኛ አገዛዝ ለማላቀቅ አደርጎ መገመት  ቢያንስ የፖለቲካ ተላላነት ይሆናል።

ስለሆነም የወደፊቱ ህብረት አስቀድሞ ወዳጅ ማን ነው ጠላትስ? እንዲሉ በሰሞኑ በግራዚያኒ መንግሥቱ መጽሐፍ ዙሪያ የተነሳው የደርግ ትኩሳት አስተምሮነቱን ያስተውሏል።